# የኢትዮጵያን ሰፊ መሬት ለሱዳን ለማስረከብ ወያኔ ሽር-ጉድ ይዟል

## ከኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ

ታኅሣሥ 22 ቀን 2002 ዓ. ም.
December 31, 2009

የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ በተለያዩ ጊዜያት እንደገለፀው ርዝመቱ 1600 ኪሎ ሜትርና የጐን ስፋቱ ደግሞ ከ30 እስከ 60 ኪሎ ሜትር የሆነውን ከሑመራ እስከ ጐሙ ጉፋ ድረስ የተዘረጋውን፤ የማዕድን ቦታና ውሃ ገብ ለም መሬት ለሱዳን ለማስረከብ በወያኔና በሱዳን መንግሥታት መካከል ሞቅ ባለ መንገድ ሽር ጉድ መባል ከተጀመረ ሰንብቷል። ራሱን "የሱዳንና የኢትዮጵያ የብልፅግናና የድንበር ኮሚሽን" ብሎ የሚጠራው ኮሚቴ 12ኛውን ጉባዔ ከታኅሣስ 19 ቀን 2002 ዓ. ም. (December 28, 2009) ጀምሮ በመቀሌ ውስጥ በማካሄድ ላይ ይገኛል። የአሁኑን ስብሰባ ልዩ የሚያደርገው (1ኛ) መቀሌ የስብሰባው ማዕከል መሆኑ፣ (2ኛ) በጉባዔው የሚሳተፉት የኮሚቴው አባላት ብቻ ሳይሆን ብዙ ቁጥር ያላቸው ከፍተኛ ባለሥልጣናት ከሁለቱም በኩል መኖራቸውና (3ኛ) የኢትዮጵያን መሬት ርክክብና አሸኛኘት ለማጀብ የተሰባሰበው የሁለቱም ወገኖች የዘፋኝና የሙዚቃ አባላት ብዛት ነው።

በዚህ ስብሰባ በሱዳን በኩል 135 ባለሥልጣናት ሲገኙ ከ40 ያላነሱ የሙዚቃ ባንድ አባላት አጅበዋቸዋል። በወያኔ በኩል አብዛኛዎቹ በፀጋዬ በርሄ የሚመሩ የትግራይ ክልል ባለሥልጣናት ሲሆኑ፤ አጫፋሪዎቹ ደግሞ ከአማራ፣ ከቤንሻንጉልና ግሙዝ እንዲሁም ከጋምቤላ ክልሎች የተውጣጡ ወኔ የከዳቸው አድርባዮች ናቸው።

ምንም እንኳ የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያ መሬት ተቆርሶ ለሱዳን መሰጠቱን ደግፎ ተሰለፈ፣ ዳንኪራ ረገጠ ብሎ ለማመን ቢያስቸግርም፤ ወያኔ የትግራይን ሕዝብ ተጠቅሞ የሚያከናውነውን ተንኮል የአሁኑ የክህደት ጉባዔ መድረክ የበለጠ አጉልቶታል። የሱዳን ባለሥልጣናት ሰኞ ታህሣስ 19 ቀን 2002 ዓ. ም. (December 28, 2009) መቀሌ በገቡበት ሰዓት የከተማው ሕዝብና ተማሪዎች ወጥተው ባንዴራ በማውለብለብ በጭፈራና በመዝሙር የአደረጉላቸው የአቀባበል ድምቀት በአለፈው ዓመት የሱዳኑ ፕሬዚዳንት አል በሽር መቀሌን በጎበኙበት ጊዜ ከተደረገለት አቀባበል የላቀ ነበር ተብሏል። ይህ ደግሞ ሆን ተብሎ የተደረገ ትርኢት ነው።

መቀሌም ለዚህ ጉባዔ ማዕከል እንዲሆን መመረጡ አጋጣሚ አይደለም። በድንበር አካባቢ ያሉ ወገኖቻችን "ቤተሰቦቻችን የት ይደርሳሉ? የትስ አርሰንና ከብቶቻችንን አሰማርተን እንኖራለን?" ብለው በጭንቀት በየበርሃው በሚባዝኑበት በአሁኑ ወቅት የትግራይ ሕዝብ ወራሪዎችን እያወደሰና እየጨፈረ እንዲቀበል ማድረግና ያን ትርኢት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ማቅረብ ምን ያህል መለስ ዜናዊ የትግራይን ሕዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ለማቀያየምና ለማዳማት የሚያደርገው ከፍተኛ ሴራና ወንጀል ልዩ ምዕራፍ የያዘ መሆኑን ነው።

የመለስ ዜናዊ ሌላው አስነዋሪ ባሕሪው በውጭ አገር ከፍ ብሎ መታየትና ከሀብታም አገሮች የሚገኘውን የንዋይ ፍርፋሪ ለመለቃቀምና ርካሽ ዝናን ለማግኘት ሲል የአገርን ጥቅም በቀላሉ መቸርቸርና ከዚያም ወደ አገር ቤት ሲመለስ በራሱ ሕዝብ የቦዘኔና የብልግና ቃላት በመወርወር መደንፋት ነው። ይህ አስፋሪ ባሕሪው በአለፈው በዴንማርክ ርዕሰ ከተማ ኮፐንሀገን በተደረገው ስብሰባ ለዓለም ሕዝብ ይፋ ሆኗል። ውሸት በመደጋገምና ቁርጠና መስሎ በመታየት የተታለሉት የአፍሪካ አገሮች፤ ለአፍሪካ ጥቅም ተሟጋች አድርገው ቢወክሉት ከፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ጎን ቆሞ

*ለመታየትና ከዚያም ከምዕራቡ ዓለም የሚወረወርለትን ፍርፋሪ ለመለቃቀም ሲል ብቻ አፍሪካውያን የጣሉበትን አደራና እምነት ክዶ አፍሪካን ለከፍተኛ ጥቃት ሲአጋልጣት መላው ዓለም ለማየት በቅቷል። መከረኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ለመለስ ዜናዊ የክህደት ባሕሪ ከተዳረገ ከ*18 *ዓመት በላይ አስቆጠሯል።*

*የዚህ የክህደት ባሕሪው በቅርቡ የወለደው አዲስ ክስተት ደግሞ ድሃ ወገኖቻችንን ከቤታቸውና ከመንደራቸው ማፈናቀል ነው። ከ*50 *ዓመት በላይ "መሬት ለአራሹ" በሚለው የትግል መርሕ ብዙ ሽህ ኢትዮጵያውያን ተሰውተው ለድህው ገበሬ የተመለሰውን የደቡብ፣ የመካከልና የምስራቅ ኢትዮጵያ ለም መሬት ወያኔ ለአረብና ለኢስያ ከበርቴዎች ከ*40 *እስከ* 100 *ዓመት በሚደርስ የኮንትራት ጊዜ እየቸረቸረ ወገኖቻችንን ለአዲስ ቅኝ ገዥዎች* (Neo-Colonialists) *ጭሰኛ እያደረጋቸው ይገኛል። ይባስ ብሎ ደግሞ ወደፊት ለአገርና ለወገን በማዕድን፣ በዘይት ሀብትና በእርሻ ተስፋ የሆነውን መሬት ለሱዳን ቆርሶ ለመስጠት ሌት ከቀን እየሠራ ይገኛል።*

*ይሁንና የወያኔ የገዥ ቡድንና የሱዳን መንግሥት እንዲያውቁት የሚፈለገው፤*

1ኛ/ *የኢትዮጵያ ሕዝብ በስተጀርባው የሚደረግና የራሱን ጥቅም የማያስጠብቅ ምንም ዓይነት ስምምነት በፍጹም አይቀበልም። አሁንም ይሁን ወደፊት በሕግም ይሁን በኃይል መሬቱን ለማስመለስ መብቱ የተጠበቀ ነው።*

2ኛ/ *ሕዝብ አያውቅም፣ "እኔ ታዛዥ ነኝ" በሚል ግብዝ ምክንያትና በጊዜያዊ ጥቅም ታውረው በዚህ የአገርን ከፍተኛ ጥቅም አሳልፎ በሰጠ ስምምነት የተሳተፉ፣ ድርጊቱን በመቃወም ፈንታ በአካልም ሆነ በፊርማ ወይም በሁለቱ መንገድ የተሳተፉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በግልም ሆነ በጋራ፣ በታሪክና በሕግ ፊት በአገር ክህደት ወንጀል ተጠያቂ መሆናቸውን አጥብቀው ሊገነዘቡት ይገባቸዋል።።*

## *ውድ ኢትዮጵያውያን ሆይ*!

*ወያኔ በአገራችን ላይ የሚያደርገው ከፍተኛ ክህደትና ሴራ ረገብ ማለት አልቻለም። ሌሎቻችን ደግሞ የአለፉት አባቶቻችንና እናቶቻችን በብዙ መስዋዕትነት ያስተላለፉልንን አገር ለሚቀጥለው ትውልድ የማስተላለፍ ግዴታ አለብን። ለዚህም ተቀዳሚው ተግባር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሆነ ኢትዮጵያዊት በግልም ሆነ በጋራ የወገናችንን ስቃይና መከራ ከዚያም የወያኔን የክህደት ወንጀልና መሠሪነት ጠልቆ ሊሰማን ይገባል። ከዚያም በማከታተል በምንችለው መንገድና ቀዳዳ ሁሉ ለሌሎች ኢትዮጵያውያንና ለዓለም አቀፍ ተቅዋማትና መንግሥታት የሕዝባችንን እሮሮ በጉልህ ማሰማት ይገባናል። እነዚህን የትውልድ ግዴታዎች እያንዳንዳችን እንድንወጣ የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ ከፍተኛ ጥሪ ያቀርባል።*

## *ኢትዮጵያ በልጆቿ ቆራጥ ተጋድሎ ትከበራለች*!

*የኢትዮጵያ ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ*
Ethiopian Border Affairs Committee
P.O. Box 9536, Columbus, Ohio 43209, USA
e-mail:- ethiopianborders@gmail.com